# የአግሮ ቢግ ፕሮግራም
# የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ

# መመሪያ

ህዳር 15፣ 2012 ዓ.ም
ባህር ዳር

# የይዘት ማውጫ

1. **መግቢያ** ........ 3
2. **የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ዓላማዎች** ........ 3
   2.1 ለድጋፍ የሚያመለክቱ አካላትና የሚደረገው ደጋፍ ........ 3
3. **የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት** ........ 4
   3.1 ማመልከቻውን ማቅረብ/ማስገባት ........ 4
   3.2 የግምገማ ሂደት ........ 5
4. **የድጋፍ ፕሮጀክት አፈጻጸም** ........ 7
   4.1 የባንክ ሂሳብ ስለመክፈት ........ 7
   4.2 የድጋፍ በጀት ፍሰት/አለቃቅ ........ 7
   4.3 የግዥ ስነስርዓት እና የሰነዶች አያያዝ ........ 7
   4.4 የሩብ አመት የሂደት ሪፖርቶች ........ 7
   4.5 ክትትል ........ 7
5. **የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ** ........ 8
   5.1 የፕሮጀክቱን ፋይል መዝጋት ........ 8

**<u>አህጽሮተ-ቃላትና ምህጻረ-ቃላት</u>**

የገኢ.ልትቢ. - ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ቢሮ
የፕድዩ - የአግሮ ቢግ የፕሮግራም ድጋፍ ዩኒት
የወገኢ.ልጽ - የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት
የወስኮ - የወረዳ ስቲሪንግ ኮሚቴ
የወቴኮ - የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ

# 1. መግቢያ

አግሮ ቢግ በኢትዮጵያ እና በፊንላንድ መንግስታት የሚደገፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ቢሮ አስተባባሪነት የሚተገበር ግብርና ተኮር የንግድ ልማት ፕሮግራም ነው፡፡ የፕሮግራሙ ዓላማ ግብርና ተኮር የኢኮኖሚ እድገት በማምጣት ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡

የአግሮ ቢግ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም በአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ አቸፈር፣ ሰሜንና ደቡብ ሜጫ፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ ደራ ፣ ፎገራና ሊቦ ከምከም ወረዳዎች የአነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮችን በግብርና ተኮር ንግድ ልማትን ይደግፋል፡፡ ፕሮግራሙ የሚደገፋቸው ዘርፎች በሽንኩርት፣ ድንች፣ ሩዝ፣ በቆሎ፣ ዶሮ እርባታ፣ ፍየልና በግ ማደለብና የወተት ተዋጽኦ ልማት ናቸው

# 2. የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ዓላማዎች

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ዓላማ በእሴት ሰንሰለት ላይ ተሳታፊ አካሎች የገንዘብ እና ገንዘብ ነክ አገልግሎቶች አግኝተው እሴት በመጨመር በንግድ ልማት ተወዳዳሪነታቸው በማሳደግ እና ተቋማዊ ዘላቂነታቸው እንዲረጋገጥ ማገዝ ነው። አዳዲስና የተሻሻሉ አሰራሮችና የፈጠራ ሀሳቦች ይበረታታሉ። አዳዲስና የተሻሻሉ አሰራሮችና የፈጠራ ስራዎች/ሀሳቦች ሲባል ለአካባቢው አዲስ የሆነ ወይንም ለየት ያለ የአሰራር ሞዴል፤ የማምረቻ ቴክኖሎጂና የአሰራር ስልት ወዘተ ለማለት ነው።

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንዱ ከአግሮ ቢግ የእሴት ሰንሰለት የተያያዙ መካከለኛ የግብርና ተኮር ንግድ ልማት ኢንቨስትመንቶችን ለመደገፍ ያለመ ሲሆን በዋናነት የሚከተሉትን ዝርዝሮችን ያካተተ ቢሆንም በነዚህ ግን የተወሰነ አይደለም፡-

- የገበያ ትስስርና ዘዴን የሚያጎለብት፣ የገበያ አዉታርን ማጎልበት፤ አቅርቦትን፤ በኮንትራት ግብይት፤ አዲስ የገበያ ማስፋፋት ፤
- የድህረ ምርት አያያዝ፤ መጋዘን/ የእህል ማከማቻ አስተዳደር፣ ማጽዳት፣ ልየታና ደረጃ ማውጣት ያሉ፤ በጥራትና በብቃት የግብርና ምርቶችን ማቀነባበሪና ቁሳቁሶች አያያዝና አጠቃቀም፤ ማሸግንና ቀዝቃዛ መጋዝን ትኩረት ያደረገ፤
- የዩኔየኖችንና የማህበራትን አባላት አቅምና አገልግሎት ሊያሻሽሉ የሚችሉ፤
- የደሮ መኖ ማቀነባበርና የተደረሽነት እሴት ሰንሰለት ማሳደግ

## 2.1 ለድጋፍ የሚያመለክቱ አካላትና የሚደረገው ደጋፍ

**ማመልከት የሚቸሉ አካላት**

- የህብረት ስራ ማህበራትና ዩኔየኖች፣ የዘርፍ ማህበራት ፤ የተመዘገቡ/ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው ድርጅቶች ሲሆኑ አመልካቾች ቢያንስ ለአንድ ዓመት በአግሮ ቢግ የእሴት ሰንሰለት በተመረጡ ዘርፎች የሰሩ ወይንም ስራቸውን በእነዚህ የእሴት ሰንሰለት ማስፋፋት ፍላጎቱ ያላቸው፤
- አመልካቾች አግሮ ቢግ ባቀፋቸው ወረዳዎች ማለትም በሰሜንና በደቡብ አቸፈር፣ በሰሜንና በደቡብ ሜጫ፣ በባህር ዳር ዙሪያ፣ ደራ ፣ ፎገራና ሊቦ ከምከም የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡ በወረዳዎች ውስጥ ያሉ ከተሞችን የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም የዞን ከተሞች ባህር ዳር ደብረታቦርና ፍኖተ ሰላም ያካትታል፡፡

**የመቀናጀ ድጋፍ**

- ከፍተኛው የድጋፍ መጠን 1 ሚሊዮን ብር
- ዝቀተኛው የድጋፍ መጠን ብር 150,000
- የፕሮጀክቱን 50 በመቶ የሚሆነውን የተዛማጅ ፈንድ መጠን ከአመልካቹ ይጠበቃል፤
- አንድ አመልካች ከአንድ ጊዜ በላይ ማመልከት አይፈቀድለትም፤
- በሴቶች ባለቤትነት የሚከናወን የቢዝነስ ተቋምና የህብረት ስራ ማህበራት ቢያንስ 50 በመቶ አባሎቻቸው ሴቶች ከሆኑ 50 በመቶ የሚሆነውን ተዛማጅ ፈንድ በአይነት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዓይነት ለሚያቀርቡት የንብረት ማረጋገጫ መረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

- በሴቶች ባለቤትነት የሚከናወን የቢዝነስ ተቋምና እና የህብረት ስራ ማህበራት ቢያንስ 50 በመቶ አባሎቻቸው ተጨማሪ ነጥብ ያገኛሉ፤
- የአካል ጉዳት ባለባቸው ሰዎች የሚያቀርብ ወይም እነሱን ትኩረት ያደረጉ ፕሮፖዛሎች ተጨማሪ ነጥብ ያገኛሉ፤
- የሚቀርቡት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ጥበቃ ዘላቂነትንና ሊያደርሱት የሚችሉትን አካባቢያዊ ብክለትን በተመለከተ በፕሮፖዛላቸው ውስጥ ማካተት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ፕሮጀክቱ ምንም ዓይነት ጉዳት የማያደርስ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ድጋፍ የሚደረግላቸው ፕሮጀክቶች የመጨረሻ የአፈፃፀም ጊዜ ስሌዳ እስከ ሰኔ 22 ቀን 2013 አመተ ምህረት ድረስ መሆን አለበት፤
- የቀረበው ፕሮፖዛል የመስሪያ ቦታን ወይም መሬት ማግኘትን የሚጠይቅ ከሆነ ፕሮፖዛሉ በሚቀርብበት ጊዜ ቦታው/መሬቱ ለመገኘቱ ማረጋገጫ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
- የአቅም ግንባታ ስራዎች የፕሮጀክቱ አካል ሆነው መቅረብ ይችላሉ፤
- ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ወጭዎች እና በድጋፍ በጀት ላይ ያልተገለጹ ወጭዎች ተቀባይነት የላቸውም:
- በፕሮጅክቱ መካተት የሌለባቸው ወጭዎች፡- የሰራተኛ ደመወዝ፤ መደበኛ የሆኑ አስተዳደራዊ ወጭዎች (እንደ ኪራይ፤ የኤሌክትሪክና የዉሃ ወጭዎች፤ ወዘተ)፤ የብድር/ወለድ ክፍያ፤ የተሽከርካሪ ግዥና የመሬት/ቦታ ግዥ፤

## 3. የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት

የመቀናጀ ፈንድ የማስተዋወቁ ስራ በበኩር ጋዜጣ፤ በወረዳው የገንዘብና ኢኮኖሚክ ትብብር የማስታዎቂያ ቦርዶች፤ ባህር ዳር በሚገኘው የአግሮ ቢግ ጽ/ቤት እና በአግሮ ቢግ በይነ መረብ/ቄብ ሳይት አድራሻ ማለትም በ www.agrobig.org እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ይህ መመሪያ ባህር ዳር በሚገኘው አግሮ ቢግ ቢሮና በየወረዳዎቹ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ጽ/ቤቶች መውሰድ ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር ኤልክትሮኒክ ኮፒ አግሮ ቢግ ቄብ ሳይት ላይ ማውረድ ይቻላል፡፡

የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ (ኮንሴፕት ኖቱን) እንዲሁም ሙሉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ከመቅረቡ በፊት አመልካቾችን ሊያግዙ የሚችሉ ድጋፍ (help desks) የሚሰጡ ባለሙያዎች የወረዳው ገንዘብ፤ ፋናንስ ትብብር ጽ/ቤት ሃላፊነት ይሰጣል፡፡ የድጋፍ ሰጭ አካላት ዋና ስራቸው እንደ አግባቡ አመልካቾች የመቀናጀ ፈንድ መመርያውን መከተላቸውን፤ የተጠየቀውን ትክክለኛ ፎርማቶችን መጠቀማቸውን፤ አስፈላጊ ዶክመንቶች መሟላታቸውንና በትክክል መፈረሙን እገዛ ያደርጋሉ፡፡

የፕሮፖዛል አቅራረቡ ሁለት ደረጃዎች/ሂደቶች አሉት የፕሮጀክት ሀሳብ (ኮንሴፕት ኖት) -(አባሪ 1ን ይመልከቱ)፡፡ ከቀረቡት የፖሮጀክት ሃሳቦች (ኮንሴፕት ኖት) መካከል ከፍተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ ወደ ሁለተኛው ደረጃ ማለትም ሙሉ ፕሮጅክት ፕሮፖዛል እንዲያቀርብ ይጋበዛሉ (አባሪ 2ን ይመልከቱ)፡፡

### 3.1 ማመልከቻውን ስለማቅረብ/ማስገባት

አመልካቾች ኮንሰፕት ኖቶቱንና የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን ሸኝ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ አብዛኛው ስራበሚፈጸሙባቸው ወረዳዎች ለሚገኙ የወረዳ ፋይናንስና የኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዞን ከተማ ያሉ አመልካቾች የሚከተለውን አማራጭ መጠቀም ይችላሉ፤

- ደብርታ ቦር ያሉ ፕሮጀክቶች አብዛኛው ስራ ለሚፈጸምባቸው ወረዳዎች ሊቦ ከምከም/ፎግራ/ ድራ ፋይናንስ የዒኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች
- በተመሳሳይ ፍኖተ ሰላም ያሉ አመልካቾች ሰሜን/ደቡብ ሜጫ/ሰሜን/ደቡብ አቸፈር/ባህር ዳ ዙሪያ ማመልከት ይችላሉ፡፡

በታሸገ ፖስታ የመቀናጀ ፍንድ /Matching Grants/ በማለት ለሚመለከተው ባለሙያ ወይንም መዝገብ ቤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ለሁለቱም (ኮንሴፕት ኖትም ሆነ ፕሮፖዛሉ) የእንግሊዘኛ ወይንም አማረኛ ቋንቋ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ማምልከቻው ስለመግባቱ መረጃ ይሆን ዘንድ በቀሪ ሸኝ ደብዳቤ ላይ የተቀበለው አካል ፊርሞ ማህትም እንዲያደርግላቸው ይሆናል፡፡

በማስታወቂያ ከተገለጸው ቀን አልፎ የመጣ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሁሉም ኮንሰፕት ኖቶችም ሆነ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን የወረዳ ፋይናንስና የኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ቢያንስ አንድ ከ አግሮቢግ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት ተወካይ ባለበት ፖስታዎች የሚከፍቱ ይሆናል፡፡

## 3.2 የግምገማ ሂደት

የቀረቡ ኮንሴፕት ኖቶችና ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማና መረጣ ላይ የሚሳተፉ ግለሰቦች ምንም ዓይነት መድልኦ ላለማድረግና የመጨረሻው ውጤት በይፋ እስኪነገር ድረስ ሚስጥር ለመጠበቅ **በአባሪ 3** መሰረት ፊርማ በመፈረም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

እያንዳንዱ ኮንሴፕት ኖት በ3 ገምጋሚዎች የሚታይ ሆኖ ስብጥራቸውም፤

- 1 ኮንሴፕት ኖቱ በቀረበበት ወረዳ የተወከለ፤
- 1 ተወካይ ከወረዳው ህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ወይም ከወረዳው የንግድ ዘርፍ ማህበራት፤
- ሶስተኛው በአግሮቢግ የፕሮግራሙ ማስተባበሪያ ዩኒት የሚወከል ይሆናል፡፡

  ገሚጋሚዎቹ በአባሪ 4 የተቀመጡትን የመገምገሚያ መስፈርቶች የሚጠቀሙ ይሆናል፡፡ የማመልከቻ ቅፁን ከተጠየቀው ገጽ በላይ ያቀረቡ ወይንም በትክክል ያልተጠቀሙ አመልካቾች ዝርዝሩን ማየት ሳያስፈልግ ውድቅ ይደርጋሉ፡፡ ገምጋሚዎቹ ለእያነዳንዱ ኮንሴፕት ኖት ፕሮፖዛሉን በተናጥል ውጤት ከሰጡ በኋላ የገምጋሚዎቹን አማካይ ውጤት በመውሰድ ዉጤቱ ይሰላል፡፡ ይህንን ዉጤት መሰረት አድረጎ ወደ ሁለተኛ ደርጃ ያለፉትን ኮንሴፕት ኖቶች ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ በወረዳ የፍይናንስና ኢኮኖሚክ ትብብር ጽ/ቤት በኩል ጥሪ ይደረግላቸዋል፡፡

ሙሉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲያቀረቡ ለተመረጡ አመልካቾች በፕሮፖዛል ዝግጅት ዙሪያ (ዓላማ፣ ዝርዝር ተግባራት፣ተጠቃሚዎች እንማን መሆን እንዳላባቸው፣ የግዥ አፈጻጸም፤ በጀት ስሌትና ፍሰት፤ ሪፖርት አደራረግ፤ ዶክመንት አያያዝና ክትትልን በተመለከተ ገለጻ/ኦሬንቴሽን ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ኦሬንቴሽን ስልጠናው በወረዳዎቹ ዋና ከተሞች የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ፕሮጅክቱን የመቅረጽና የዝግጅት ስራው ሙሉ በሙሉ የአመልካቾች ሓላፊነት ነው፡፡ የፕሮጅክት ማቅረቢያ ቅጽ (አባሪ 2)ን ያልተከተሉና በተወስነው የማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ያለቀረበ ማመልከቻ ውድቅ ይደረጋሉ፡፡

የቀረቡት ፕሮጅክት ፕሮፖዛሎቹ በ5 የገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ውጤት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

- ሁለቱ ኮሚቴዎች ፕሮጀክቱ በቀረበበት ወረዳ የሚወከሉ የኮሚቴ አባላት ይሆናሉ
- ሁለት ቋሚ አባላት ከክልል ገበያ ልማትና ንግድ ቢሮ እና ከክልል ህብረት ስራ ኢጀንሲ ወይም ከንግድ ዘርፍ ማህራት የሚውከሉ ይሆናሉ
- አምሰተኛው አባል ከአግሮ ቢግ የፕሮግራሙ ማስተባበሪያ ዩኒት የሚወከል ይሆናል፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ገምጋሚ ኮሚቴው ለተጨማሪ ሙያዊ ትንትና እና ድጋፍ ባለሙያተኞችን ሊጋብዝ ይችላል፡፡

ኮሚቴው በአባሪ 4 ላይ የተመላከተውን የመገምገሚያ መስፈርት በመጠቀም ፕሮጀክቱን ይገመግማል፡፡ ኮሚቴው የመስክ ጉብኝት በማድርግ በፕሮፖዛሉ ላይ የተካተቱትን መረጃዎች ለማረጋገጥ እና

የአመልካቹን አቅም መፈተሽ የግምግማው አካል ማድርግ የግድ ነው፡፡ በተጨማሪም የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን ሃሳብ አመልካቹ ወይንም ለአመልካቹ ድርጅት የሚሰራ አካል ለኮሚቴው እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ የገምጋሚዎችን ዉጤት መሰረት በማድረግ  አማካኝ ውጤት ተሰልቶ የአመልካቹን ውጤት የሚወስኑት ሆኖ በደረጃ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

ኮሚቴው ጠቅላላ ውጤቱ በግልፅ በማሳየት ምክረ ሀሳቡን ለአግሮ ቢግ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት ይልካል፡፡ ምክረ ሀሳቡ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፤

ሀ. ፕሮፖዛሉ ድጋፍ ቢሰጠው ጠቃሚ መሆኑን የሚገልፅ፤
ለ. ፕሮፖዛሉ በተጠባባቂነት ድጋፍ የሚያገኝ ቢሆን፤
ሐ. ፕሮፖዛሉ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ እንዲሆን የሚል፤

አግሮ ቢግ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ዩኒት የውጤት አሰጣጡን ሂደትና የበጀት መጠኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ለመቀናጆ ፍንድ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ከተመረጡት ፕሮጀክቶች ውስጥ መቀናጆውን ማዋጣት ያልቻለ ወይንም ሂደቱን ማቋረጥ የሚፈልግ ቢኖር ተጠባባቂ ፕሮጀክቶችን በመጨመር የፕሮግራም ማስተባባሪያ ዩኒት ምክረ ሃሳቡን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ይልካል፡፡

የድጋፍ ፈንድ አሸናፊዎች ውጤቱ በጹሁፍ እንዲገለጽላቸው ተደርጎ በ30 ቀናት ውስጥ በሚመለከተው የወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ቀርበው ውል እንዲወስዱ ውሳኔው ይነገራቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በ30 ቀናት ውስጥ ቀርበው ውል ካልወሰዱ ድጋፉ ይሰረዝባቸዋል፡፡ ፕሮፖዛሎቻቸው ያልተመረጡላቸው አመልካቾች ያቀረቧቸው ፕሮፖዛሎች እንዳልተመረጡ ይገለጽላቸዋል፡፡ ነገር ግን ኮንሰፕት ኖቶቹ እና ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎቹ ለአመልካቾቹ ተመላሽ አይደረጉም፡፡

የድጋፍ ገንዘብ የተለቀቀላቸው ፕሮጀክቶች ርዕሶች፣ የድጋፍ ተቀባይ ስም፣ ፕሮጅክቱ የሚገኝበት ቦታ እና የድጋፍ ገንዘቡ መጠን በሚመለከተው የወረዳ ጽ/ቤትና በአግሮ ቢግ ዌብ ሳይት www.agrobig.org በግልጽ ይለጠፋል፡፡

ጠቋሚ የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ በታች ቀርቧል ሆኖም ግን እንዳመልካቹ ብዛት የጊዜ ሰሌዳ ሊቀየር እንደሚችል መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የጊዜ ሰሌዳ ለውጥ ካለ ወረዳው በማስታወቂያ ያሳውቃል፡፡

| **በማመልከቻ አቀራረብና የግምገማ ሂደት የጊዜ ሰሌዳ ቢጋር** | **የጊዜ ሰሌዳ** |
|---|---|
| ማስታወቂያ ማውጣትና ፍላጎት ያለቸውን አካላት ጥሪ ማድረግ | ህዳር 21፣ 2012 |
| ማመልከቻ የማቅረቢያ የመጨረሻው ጊዜ | ታህሳስ 21፣2012 |
| ኮንሴፕት ኖቱን መገምገምና ሙሉ ፕረጀክት ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ መጋበዝ | ጥር 22፣ 2012 |
| ሙሉ ፕሮጀክት ፕሮፐዛል ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን | የካቲት 20፣ 2012 |
| ፕሮፖዛሉን መገምገም የተመረጡና ተጠባባቂ አመልካቾች ዝርዝር መለየትና ለማስተባበሪያ ዩኒት ማቅረብ | መጋቢት7፣ 2012 |
| የፕሮገራሙ ማስተባባሪያ ዩኒትና ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የመቀናጆ ፈንድ አሸናፊዎችን ለወረዳ ማሳወቅ | መጋቢት21፣ 2012 |
| ወረዳው ለአሸናፊዎች ማሳወቅና የውል ስምምነት እደንዲፈርሙ ማመቻቸት (አሸናፋች የባንክ አካውንትና ሌሎች መሙላት ያለባቸውን እንዲያሟሉ ማደረግ) | |
| ሌሎች ዝርዝር ስራዎች በስምምነቱ የሚካተቱ ሆኖ ፤<br>- የተመረጠው የፈንዱ ተጠቃሚ የሚጠበቅበትን መቀናጆ ወደባንክ አካዉንቱ ማስገባት<br>- የክልሉ ገንዘብና ኢ/ል/ት/ቢ.ሮ የመጀመርያ ደረጃ ክፍያን ወደሚመለከተው የወረዳ ገ/ኢ/ል/ት/ፅ/ቤት ማስገባት<br>- የወረዳው ገ/ኢ/ል/ት/ፅ/ቤት የመጀመርያ ደረጃ ክፍያን ወደሚመለከተው የፈንዱ ተጠቃሚ አካውንት ማስገባት<br>- ዝርዝር የፕሮጀክቱ ትግበራ ቢጋር ማዘጋጀት | ከመጋቢት 30፣ ጀምሮ |

## 4. የድጋፍ ፕሮጀክት አፈጻጸም

የድጋፍ ውሉ (አባሪ 5) በሚመለከተው የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት እና በአመልካቹ/ድጋፍ ተቀባዩ መካከል ይፈረማል፡

### 4.1 የባንክ ሂሳብ ስለመክፈት

ድጋፍ ተቀባዮች በስማቸው ከሚፈልጉት ባንክ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ወይም ቀድሞ ካላቸው ዝርዝሩን ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በደብዳቤ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ማለት የሂሳብ ቁጥሩ ኮንትራቱን ለመፈረም የተሰጠው 30 ቀናት ከማለቁ በፊት ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዝርዝር ፕሮጀክቱን የሚመለከቱ ማናቸውም የባንክ እንቅስቃሴዎች በዚህ የባንክ ሂሳብ ይከናወናሉ፡፡

ድጋፍ ጠያቂዎቹ ለፕሮጀክቱ የሚያደርጉትን የመቀናጆ ፈንድ ድርሻ የሚያገኙት የድጋፍ ገንዘብ ወደ ሂሳባቸው ከመተላለፉ በፊት በባንኩ ሂሳብ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ምንዓልባትም ድጋፍ ጠያቂው የራሱን ድርሻ ኮንትራቱን በተፈረመ በ60 ቀናት ውስጥ በዝግ አካውንት አስገብቶ ከባንኩ ማረጋጫ ካላቀረበ ወይም ማስገባት ካልቻለ ኮንትራቱ ይሰረዛል፡፡

### 4.2 የድጋፍ በጅት ፍሰት/አለቃቀቅ

የድጋፍ ገንዘብ አለቃቀቁ እንደየፕሮጀክቶቹ ሁኔታ የሚለያይ ሆኖ በድጋፍ ውሉ ላይ በግልጽ መስፈር ይኖርበታል፡፡ የድጋፍ ፈንድ መጠየቂያው በአባሪ 6 በመጠቀም ሲቀርብ በአባሪነት የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴና የፋይናንስ ሪፖረት በአባሪ 7 ና 8 አብሮ መቅረብ ይኖርበታል። የቅድሚያ ክፍያው እንደ ፕሮጀክቱ ባሀርሪይ የሚለያይ ሆኖ ቢበዛ የፕሮጀክቱ 80 በመቶ የሚሆነው ገንዘብ በመጀመሪያ ክፍያ ሊለቀቅ ይችላል፡፡ የድጋፍ በጀት የአለቃቅ ሂደት በኮንትራት ውሉ በግልጽ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

### 4.3 የግዥ ስነስርዓት እና የሰነዶች አያያዝ

ድጋፍ ተቀባዩ ማናቸውንም ግዥዎች በራሱ የማከናወን ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን የግዥ ሂደቶቹ ተቀባይነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡ በተቻለ መጠን ድጋፍ ተቀባዩ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች ቢያንስ 3 አባላት ባሉበት የግዥ ኮሚቴ ቢከናውን ይመረጣል፡ ከ2500 ብር በላይ የሚያወጣ ግዥ በሚያከናውንበት ጊዜ ቢያንስ ከ3 ቦታዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ መሰብሰብ ይኖርበታል፡ ፡ ድጋፍ ተቀባዩ የተፈቀደለትን የድጋፍ ገንዘብ በአግባቡ እና ግልጽ በሆነ መንገድ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት፡

ድጋፍ ተቀባዮች የፕሮጀክቱን ገቢ እና ወጭዎች የሚያሳይ ትክክለኛ የሂሳብ ሰነድ አዘጋጅተው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርቡት የፋይናንስ ሰነዶች የድጋፍ ገንዘቡን ወጭ እና ገቢ ሂሳብ ከነዝርዝር ሰነዶቹ (የባንክ ስተትመንት፣ የግዥ ሰነዶች፣ የዋጋ ማቅረቢያዎች (ፕሮፎርማዎች)፣ የግዥ ኮሚቴ ቃለጉባኤዎች፣ ደረሰኞች እና ኢንቮይሶች) መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርቡት የሂሳብ ሰነዶች የፕሮጀክቱን የገንዘብ እንቅስቃሴ ከሌሎች ገቢዎች ለይተው ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 4.4 የሩብ አመት የሂደት ሪፖርቶች

ድጋፍ ተቀባዮች በየሩብ አመቱ ለወረዳ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት እና ለፕሮግራሙ ማስተባባሪያ ዩኒት የሂደት ሪፖርት በአባሪ 7 መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል) ፡፡ የፋይናንስ ሪፖርት ከሂደት ሪፖርቱ ጋር ተያይዞ በ(አባሪ 8) መቅረብ አለበት፡፡

### 4.5 ክትትል

የድጋፍ ፕሮጀክቱ በወረዳ ፈጻሚ አካልና በአግሮ ቢግ በኩል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ይደረግለታል፡ ፡ በክትትሉም ወቅት፤

- የፕሮጀክቱን ገንዘብ በትክክል ስራ ላይ እንዳዋለ እና የሂሳብ አያያዙ እንዴት እንደሆነ እንዲሁም ጥቅም ላይ ያዋለው ገንዘብ በሰነድ ተደግፎ መቅረብ አለመቅረቡን መከታተል፤
- የፕሮጀክቱን ቴክኒካዊ አፈጻጸም ተመልክቶ አፈጻጸሙ በተያዘለት የሂደት ግብ (ማይል ስቶን) መሰረት እየሄደ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ፤

## 5. የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ

የድጋፍ ተጠቃሚው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት በ(**አባሪ 7**) መሰረት **ያቀርባል** ፡፡ የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርቱ በአጠበ ስራዎችና የተሰሩ ቃላይሂደቱ የተገኙ ውጤቶችን አጠቃሎ ከማቅረብ ባሻገር ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ ያስገኛቸውን ውጤቶች/ለውጦች ማካተት ይኖርበታል፡፡

### 5.1 የፕሮጀክቱን ፋይል መዝጋት

የፕሮግራሙ ማስተባበሪያ ዩኒት ዋና አካውንታንት ከአግሮ ቢግ ፋይናንስ አማካሪ ጋር በመተባበር እና ድጋፍን ያገኘው አካል በጋራ በመሆን የፕሮጀክቱን ፋይል እንዲዘጋ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡ ፡ ይህን ሲያደርጉ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ሂደቶች መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡-

- ድጋፍ ተቀባዩ ያቀረበውን የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ማጽደቅ፤
- ለድጋፍ የተመደበው ገንዘብ መከፍሉና ያልተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በትክክል መፈጸማቸውን በማረጋገጥ የፕሮጀክቱን የሂሳብ ቁጥር መዝጋት፤
- በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ቢሮ የመጨረሻ ኦዲት እንዲደረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- የድጋፍ አመልካቹ ግዴታዎችን በአግባቡ እንደተወጣ በማረጋገጥ አመልካቹ ፕሮጀክቱን በአግባቡ መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ አዘጋጅቶ መስጠት፡፡ ድጋፍ ተቀባዩ ሁሉንም የፕሮጀክት ሰነዶች እና የሂሳብ መዛግብት መንግስት ለኦዲት በሚፈልግበት ጊዜ ለማቅረብ እንዲችል ለሚቀጥሉት 3 ዓመታት ተይዘው እንዲቆዩ ማሳሰብ፤
- በመጨረሻም የፕሮጀክት ማተባበሪያ ዩኒቱ ፕሮጀክት ፋይል እንዲዘጋ ማድረግ፡፡

<u>የግርጌ ማስታወሻ</u>

ይህ መመሪያ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን የአማርኛው ቅጂ በህግ ፊት የጸና ይሆናል፡፡